የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፩
አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፰ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 1
ADDIS ABABA 7th November 2013

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፺፰/፪ሺ፮ ዓ.ም.

የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ......ገፅ ፯ሺ፩፻፲፩

## CONTENTS

Regulation No. 298/2013

Public Service Employee's Transport Service Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation........ Page 7111

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፺፰/፪ሺ፮

## የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፺፰/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ "የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች" ማለት በአዲስ አበባ የሚገኙ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችን እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሥሪያ ቤቶችን ሠራተኞች ያጠቃልላል።

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 298/2013

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO ESTABLISH THE PUBLIC SERVICE EMPLOYEE'S TRANSPORT SERVICE ENTERPRISE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 47(1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Public Service Employee's Transport Service Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 298/2013".

### 2. Definition

In this Regulation "public service employees" include employees of federal government offices in Addis Ababa and the Addis Ababa City Administration offices.

፫. <u>መቋቋም</u>

፩/ የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪/ ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል።

፬. <u>ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን</u>

የትራንስፖርት ሚኒስቴር የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል።

፭. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል።

፮. <u>ዓላማ</u>

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ ለፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤

፪/ ከፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች የሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ውጪ ለሌሎች ተገልጋዮች የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤

፫/ ከዓላማው ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሌሎች ሥራዎችን ማከናወን።

፯. <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፩ ቢሊዮን (አንድ ቢሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፭ መቶ ሚሊዮን (አምስት መቶ ሚሊዮን ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል።

፰. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

፱. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

፲. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፰ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

3. <u>Establishment</u>

1/ The Public Service Employees Transport Service Enterprise (hereinafter the "Enterprise") is hereby established as a public enterprise.

2/ The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

4. <u>Supervising Authority</u>

The Ministry of Transport shall be the supervising authority of the Enterprise.

5. <u>Head Office</u>

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa.

6. <u>Objectives</u>

The objectives for which the Enterprise is established are:

1/ to provide transport service to public service employees during office opening and closing hours;

2/ to provide transport service to other users outside of office opening and closing hours;

3/ to engage in other activities related to its objectives.

7. <u>Capital</u>

The authorized capital of the Enterprise is Birr 1,000,000,000 (one billion Birr) of which Birr 500,000,000 (five hundred million Birr) is paid up in cash and in kind.

8. <u>Liability</u>

The Enterprise may not be held liable beyond its total assets.

9. <u>Duration</u>

The Enterprise is established for an indefinite duration.

10. <u>Effective Date</u>

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 7th day of November, 2013.

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት